# ለእግዚአብሔር ፍቅር

"… እኔ የሚረባህን ነገር የማስተምርህ በምትሄድባትም መንገድ የምመራህ አምላክህ እግዚአብሔር ነኝ።" (ኢሳ 48÷17)



God's Love, P.O.Box 6734 , Lee's Summit, MO, 64064. / E-mail – mtizazu@hotmail.com / Ph/Fax 816 – 246 – 9395



**የካቲት 1995 February 2003** "ልጆችሽም ሁሉ ከእግዚአብሔር የተማሩ ይሆናሉ፡ የልጆችሽም ሰላም ብዙ ይሆናል።" (ኢሳ 54÷13)

---------- አዘጋጅ መላኩ ትዕዛዙ -------------




በጥንታዊቷ በኢያሪኮ ከተማ አቅራቢያ የሚገኘ ውና÷ጌታችን ኢየሱስ ክርስቶስ አርባ ቀንና ሌሊት ከጾመ በኋላ÷በሴይጣን የተፈተነበት በረሐ ሥፍራ ይህ ነው።

# በፈተና መደሰት

—————————————————

እአአ በ1982 ዓም የሩሲያ ጠፈርተኞች 211 ቀናት በጠፈር ቆይተው ተመለሱ። በተመለሱም ጊዜ የጠፈርተኞቹ ጤና ተቃውሶ ነበረ። የማዞርና የልብ ትርታ መለወጥ ችግር ነበረባቸው። ለሳምንት ሙሉ ተነሥተው መራመድ አልቻሉም ነበር። ወደ ምድር ከተመለሱ ከወር በኋላም ቴራፒ አልጨረሱም ነበር። Atrophy የሚባል የልብና የጡንቻ መኮሳሸት (መጠውለግ) አጥቅቷቸው ነበር። ይኸውም ከመሬት ስበት ጋር እየታገለ ለመኖር የተፈጠረው አካል ስበት አልባ በሆነው በሕዋ ውስጥ ልቅ መኖሩን ስላላወቀበት የተፈጠረ ቀውስ ነው።

ይሁን እንጂ የሶቭየት ጠፈርተኞች በተከታዩ የጠፈር ጉዞአቸው ይህንን ችግር ለመወጣት መፍትሔ አገኙ። የኸውም ጠፈርተኞች በጠፈር ቆይታቸው ወቅት ብርቱ የአካል ማጠንከሪያ ልምምድ (exercise) እንዲያደርጉ ማድረግ ነው ለዚሁም (penguin suit) ፔንጉዊን ሱት የተባለ ልብስ ሠሩ። ያም የጠፈርተኛውን እንቅስቃሴ የሚቋቋምና ተግባሩን ሁሉ ከባድ የሚያደርግ ተለጣጭ የጠፈር ልብስ ነው። ልብሱም በላቦራቶሪ ሙከራ ከተረጋገጠ በኋላ በተከታዩ የጠፈር ጉዞ ሥራ ላይ ዋለ።

በተከታዩ ጉዞ ጠፈርተኛው በጠፈር የቆየው ለ326 ቀናት ነበር። ይሁን እንጂ እአአ በ1987 ዓ.ም. በታህሣስ ወር÷ ወደ ዓለም በተመለሰ ጊዜ ጤናው ምንም አልተቃወሰም ነበር። ምክንያቱም የሰው አካል በምድር ላይ ከመሬት ስበት የሚደርስበትን ጫናና ክብደት በሰው ሠራሽ ጥበብ በጠፈር ውስጥ ማከናወን ስለ ተቻለ ነው።

መንፈሳዊ ነገርን አስመልክቶ ደግሞ ምንነታችንን አበክሮ የሚያውቀው አምላካችን÷ በምትፈተኑበት ጊዜ ደስ ይበላችሁ ሲል ይመረክረናል ምክንያቱም ከጠፈርምኞቹ ታሪክ ጋር ተመሳሳይ ነው። እንዲህ ይላል፡-

"ወንድሞቼ ሆይ÷የእምነታችሁ መፈተን ትዕግሥትን እንዲያደርግላችሁ አውቃችሁ ልዩ ልዩ ፈተና ሲደርስባችሁ እንደ ሙሉ ደስታ ቁጠሩት። ትዕግሥትም ምንም የሚጎድላችሁ ሳይኖር ፍጹማንና ምሉዓን ትሆኑ ዘንድ ሥራውን ይፈጽም።" (ያዕ 1÷2)

ሥራውን ይፈጽም? ፈተና ደግሞ ምን መልካም ሥራ ይፈጽማል? ይባል ይሆናል፡ ምክንያቱም ፈተና አይወደድም። በፈተና ወቅት ሙሉ እርግጠኝነት ስለሚያዳግት ነው። ፈተናውን ማለፋችንን እንጠራጠራለን። ተማሪዎች ሳለን ከክፍል ወደ ክፍል ማለፍ እንዳለብን እናውቅ ነበር። ክፍል ለማለፍም ፈተና እንደማይቀር አይጠፋንም። ሆኖም ፈተና በተባለበት ጊዜ ሁሉ መነጫነጭና መጠበብ የተለመደ ነው። ከፈተናው በኋላ ዕድገት መኖሩን ብናውቅም እንኳን በፈተና መደሰት ያቅታል። ይህም የሰው ተፈጥሮአዊ ባሕሪይ ነው። ስንፈተን የዕምነትና የተስፋ ቃል ከአፋችን ይወገዳል። ነገር ግን በጊዜው ሁኔታ ላይ ሳይሆን በተስፋ ቃሉ ላይ ሃሳባችንን ብናሳርፍ "ፍጹማንና ምሉዓን" እንሆን ዘንድ በፈተና መደሰት ይቻላል።

ዕድገት ዋጋ ያስከፍላል። አስቸጋሪ ሁኔታ ሲያጋጥምህ እግዚአብሔር በምን አኳያ ሊያሳድግህ እንዳሰበ ለመረዳት ጸልይ። እግረ መንገድህንም በጌታ ደስ ይበልህ።ጌታ እግዚአብሔር አምላካችን ሁሉን የሚገዛ÷ ሁሉም የሚታዘዙለት ታላቅ አምላክ ስለሆነ፡- በየፈተናው ምዕራፍ ቀርበው እንዲያገለግሉህ መላዕክቱን ስለ አንተ ያዛቸዋል ከምትችለውም በላይ እንድትፈተን አይፈቅድም። እግዚአብሔር ይመስገን።

# አስተሳሰብ እና ጤንነት

"ዕውነትንም ታውቃላችሁ እውነትም አርነት ያወጣቸኋል" (የዮሐንስ ወንጌል 8÷32)

ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይህን ሲል ምን ማለቱ ነው? ዕውነት ምንድን ነው? አርነትስ ምንድን ነው?

"ኢየሱስም፡- እኔ መንገድና ዕውነት ሕይወትም ነኝ፡ በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም። እኔንስ ብታውቁኝ አባቴን ደግሞ ባወቃችሁ ነበር፡ አለው።" (ዮሐ/ወ 14÷6-7)

"እንግዲህ ልጁ አርነት ቢያወጣችሁ በእውነት አርነት ትወጣላችሁ።" (ዮሐ/ወ 8÷36)

የሰው ልጅ በሙሉ በተቀዳሚ አርነት የሚያስፈልገው ከኃጢአት ቀንበር ነው። ከዚህም ጋር ተያይዞ ነፃ መወጣት የሚያስፈልገው፡- ከአሉታዊ አስተሳሰብና (negative thoughts) ከሚያስከትሉት ሁለገብ ቀውስ ነው። አሉታዊ አስተሳሰብ ከኃጢአት የሚመነጭና ከእግዚአብሔር ቃል ጋር በተቃራኒ የሚጓዝ የአስተናጋጆቹን መንፈሳዊና አካላዊ ጤንነት የሚጻረር ብልሽት ነው።

ጉንፋን እንደ ባለ ጉዳይ ይመላለስብሃል?የመጣው ተላላፊ በሽታ ሁሉ ያጠቃሃል? ልዩ ልዩ መድኃኒቶችንና ሕክምናዎችን ሞክረህ ተስኖሃል?

ይህ ከሆነ፡- ሰውነትህ ራሱን በራሱ ለመጠገን ከሚያደርገው ጥረት ጋር መተባበርን መማር ይኖርብሃል። ያም ማለት አእምሮህን ከማይረባህ ፀረ ጤና አስተሳሰብ ማንጻትና÷ በጤናማ አስተሳሰብ መሙላት ማለት ነው።

ብዙ ሰዎች የስሜታቸው ተገዥ ናቸው። ሌሎችም አያውቁትም እንጂ ያው የስሜታቸው ተገዥ ናቸው። ይሁን አንጂ "ዕውነትንም ታውቃላችሁ ዕውነትም አርነት ያወጣችኋል" እንደ ተባለው፡- መንፈሳዊውንና አካላዊውን ሥርዓት አውቆ በመከተል÷ ጤንነትን መዋጀት እና ከልክ ያለፈን የበሽታ ድግግሞሽ ማስወገድ ይቻላል።

ነገር ግን ያለማስተዋልን ልማዳዊ አኗኗር ለመቀየር ፈቃድና ቆራጠኝነት ያስፈልጋል። ምናልባት እንደ አመጋገብ÷ የሰውነት እንቅስቃሴ÷ የሥራና የዕረፍት ልማዶችን መለወጥ ያስፈልግ ይሆናል። በዚህ መልዕክት በተለይ ስለ አስተሳሰብ ማውሳት ስለምንፈልግ፡- ብልሹ ዕምነትን ጠባይንና የአስተሳሰብን ዘይቤ በመቀየር÷እነርሱም በሰውነት ውስጥ የሚፈጥሩትን ፀረ-ጤና መርዝ ማቆም ይቻላል።

ብልሹ ዕምነትና አስተሳሰብ ለደዌ ያጋልጣል። የእግዚአብሔር ቃል የሚከለክለን ብልሹ ባሕሪያት የሰውነትን ንጥረ ነገሮች በማቃወስ ፀረ-ጤና መርዝ (toxicity) እንዲፈጥር ያደርጋሉ። ለምሳሌ፡-

ንዴት÷ ፍርሐት÷ተስፋ መቁረጥ÷ መራርነት÷ቅናት÷ብስጭት÷አለመርካት÷ከንቱ ጸጸት÷ይቅር አለ ማለት ወዘተ አሉታዊ (negative) ነገሮች ስለ ሆኑ አእምሮን በማወክ የሰውነትን ኀብረ አሠራር ያቃውሳሉ። ሰውነት ራሱን በራሱ የመፈወስ ችሎታውን እንዳያከናውን ያደርጋሉ፡ ያም የደዌ መንገድ ነው።

# ፀረ ጤና አስተሳሰቦች

የሚከተሉት የእግዚአብሔርን ፍቅር÷ ደግነትና ኃይል ከሕይወታችን በማራቅ ጤንነትን ቀስ በቀስ የሚቦረቡሩ አስተሳሰቦች ናቸው።

* የእኔ ነገር ተስፋ የለውም።

* ሕክምናም ሊረዳኝ አይረችልም።

* የበደሉኝን ይቅር ማለት አይሆንልኝም::

* ሕይወቴ ተስፋ የለውም::መሞት ይሻለኛል::

* ስለሚሰማኝ ጭንቀት ምንም ማድረግ አልች ልም::

* ትዕግሥት ጠባዬ አይደለም::

* "ሰውን ማመን ቀብሮ ነው::"

* እንደ እኔ የተበደለ ማንም የለም::

* ምን ጊዜም አያልፍልኝም::

* ሰዎች አይወዱኝም::

የሚከተሉት ደግሞ ጤነኛ ያልሆኑ፥ለጤናም መቃወስ ሰውን የሚያመቻቹ ልማዶችና ባሕሪ ያት ናቸው::

* ከሰዎች መገለል፥ያለጓደኛ መሆን፥ መለየት:

* ተጠራጣሪነት::

* ከከብት የተገኘ ቅባት አዘውትሮ መመገብ፥ በቂ አትክልት አለመመገብ፥በቂ ፍራፍሬና ጥ ራጥሬ አለመመገብ::

* መድኃኒት መውሰድ ሲገባ አለመውሰድ:-

* በሐኪሞች ምክር አለመጠቀም::

* የሰውነት ማጠንከሪያን ልምምድ ችላ ማለት:

* በቂ ዕረፍት፥መዝናናትና እንቅልፍ አለማግ ኘት::

* ያለ ልክ መብላትና ብዙ መጠጥ፥ ማጨስ፥ ከትዳር ውጭ የሚሆን ግብረ ሥጋ ፥ ወዘተ::

* ንፉግነትና ከሰው ጋር በፍቅር አለመኖር::

* ከእግዚአብሔር ጋር ሐቀኛ የንስሐ ፥ የፀሎ ትና የአምልኮ ጊዜ ማጣት::

(የክርስቲያናዊ አስተሳሰብ ፈዋሽነት The Healing power of Christian mind ከሚል:-ዶክተር ዊሊያም ባክስ ከደረሱ ት መጽሐፍ ተወስዶ የተዘጋጀ)

"ወዳጅ ሆይ ፥ ነፍስህ እንደሚከናወን፥ በነገር ሁሉ እንዲከናወንልህና ጤና እንዲኖርህ እጸል ያለሁ::" (3ዮሐ መልክት፥2)

⌘⌘⌘⌘⌘⌘⌘⌘⌘

# የዓመፅ ሰውና ቁጥሩ

(ማሳሰቢያና ማስጠንቀቂያ)

"...የዓመፅ ሰው እርሱም የጥፋት ልጅ ... : እኔ እግዚአብሔር ነኝ ብሎ አዋጅ እየነገረ፡ በ እግዚአብሔር ቤት መቅደስ እስኪቀመጥ ድረስ አምላክ ከተባለው ሁሉ፥ ሰዎችም ከሚያመልኩ ት ሁሉ በላይ ራሱን ከፍ ከፍ የሚያደርገው ተ ቃዋሚ እርሱ ነው::" (2ተስሎንቄ 2፥3-5)

የዘመን ፍጻሜ ከመሆኑ በፊት፥ የቅዱሳን ዕረ ፍት ከመገለጡ በፊት፥ እግዚአብሔርም ወርዶ በሚወዱት መሐል ከማደሩ በፊት:- ከዚህ በላይ የተጠቀሰው ሰው ይገለጻል:: ይህም ሰው:-የቀደ መው እባብ፥ዘንዶው፥ አውሬው፥የዓመፅ ሰው፥ ወዘተ ተብሎ ነው በመጽሐፍ የተጠቀሰው:: የዓለም መድረክ በፍጥነት ለዚህ ሰው እየተዘጋ ጀ ነው ያለው:: እርሱም ጊዜው ሲደርስ ኃይማ ኖቶችን ሁሉ ያስተባብራል::ሐሳዊ ነቢያት ይኖ ሩታል:: ድንቅና ታምራትን በሴይጣን ኃይል ያደርጋል:: የዓለምን ችግሮች ለአንድ አፍታ በ መፍታት ብዙዎችን ያስታል: "... ቢቻላቸውስ የተመረጡትን እንኳ እስኪያስቱ ድረስ ታላላቅ ምልክትና ድንቅ ያሳያሉ::እነሆ አስቀድሜ ነገ ርኋችሁ::" (ማቴዎስ 24፥25)

እግዚአብሔር ይህን ማስጠንቀቅያና ዕድል የሚሰጥህ በምክንያት ነው:: ፍርድ ስለ አለ ነው:: ወደማይጠፋ የዘላለም እሳት መጣል ስለ አለ ነው:: ነገር ግን ማንም ይህንን ማስ ጠንቀቂያ ሳይሰማ ወደ እሳት እንዲጣል የእግዚአብሔር ፈቃድ አይደለም:: ከታላቅ ፍቅሩ የተነሣ አስቀድሞ ያስጠነቅቀናል::

"ነገር ግን ልባችሁ በመጠጥ ብዛትና በስካ ር ስለ ትዳርም በማሰብ እንዳይከብድ፥ ያ ቀንም በድንገት እንዳይመጣባችሁ ለራሳች ሁ ተጠንቀቁ: በምድር ሁሉ ላይ በሚቀመ ጡ ሁሉ እንደ ወጥመድ ይመጣባቸዋልና:: እንግዲህ ሊመጣ ካለው ከዚህ ሁሉ ለማም ለጥ፥በሰው ልጅም (ኢየሱስ) ፊት ለመቆም እንድትችሉ ስትጸልዩ ሁል ጊዜ ትጉ::" (ሉቃስ 21፥34-36)

የእግዚአብሔርን ዕውነት:-የወንጌልን መ ልዕክት እየሰሙ ያልተቀበሉ ሁሉ የሚመ ጣውን ሐሳዊ መሢሕና ምልክቱን በመቀበ ል ይገዙለታል:: ይህን ካላደረጉ ግን መግዛ ትና መለወጥ አይችሉም::

"ከዓለምም ፍጥረት ጀምሮ በታረደው በግ የሕይወት መጽሐፍ ስሞቻቸው ያልተጻፉ በምድር የሚኖሩ ሁሉ ይሰግዱለታል::ጆሮ ያለው ቢኖር ይስማ::" (ራዕይ 13፥8)

"ታናናሾችና ታላላቆችም: ባለ ጠጋዎችና ድሆችም ጌታዎችና ባሪያዎችም ሁሉ በቀ ኝ እጃቸው ወይም በግምባራቸው: ምልክት ን እንዲቀበሉ፥ የአውሬውም ስም ወይም የስሙ ቁጥር ያለው ምልክት የሌለበት ማ ንም ሊገዛ ወይም ሊሸጥ እንዳይችል ያደር ጋል:: ጥበብ በዚህ አለ::... ቁጥሩም ስድስ ት መቶ ስድሳ ስድስት ነው::" (ራዕይ 13፥16-18)

ማስጠንቀቂያው ይቀጥላል:-
"... ለአውሬውና ለምስሉ የሚሰግድ በግም ባሩም ወይም በእጁ ምልክቱን የሚቀበል ማንም ቢኖር፥ እርሱ ደግሞ በቁጣው ጽዋ ሳይቀላቀል ከተዘጋጀው ከእግዚአብሔር ቁጣ ወይን ጠጅ ይጠጣል፤በቅዱሳንም መላ እክትና በበጉ (ኢየሱስ) ፊት በእሳትና በዲ ን ይሣቀያል:: የሥቃያቸውም ጢስ ለዘላለ ም እስከ ዘላለም ድረስ ይወጣል፥ ለአውሬ ውና ለምስሉም የሚሰግዱ፡የስሙንም ምል ክት የሚቀበል ሁሉ ቀንና ሌሊት ዕረፍት የላቸውም::" (ራዕይ 14፥9-11)

# ማምለጫ

ከሚመጣው የዓመፅ ሰው ማምለጥ እንዴት ይቻላል?

"ያመነ የተጠመቀም ይድናል፥ያላመነ ግን ይፈረድበታል::" (የማርቆስ ወንጌል 16፥16)

"ኢየሱስም:- እኔ መንገድና እውነት ሕይወ ትም ነኝ: በእኔ በቀር ወደ አብ የሚመጣ የለም... አለው::" (የዮሐንስ ወንጌል 14፥16)

"በሩ እኔ ነኝ፤ በእኔ የሚገባ ቢኖር ይድናል ይገባልም:ይወጣልም መሰማሪያም ያገኛል (የዮሐንስ ወንጌል 10፥9)

"በእርሱ የሚያምን ሁሉ የዘላለም ሕይወት እንዲኖረው እንጂ እንዳይጠፋ እግዚአ ብሔር አንዲያ ልጁን እስኪሰጥ ድረስ ዓለ ሙን እንዲሁ ወዶአልና::" (የዮሐንስ ወንጌል 3፥16)

## ከዓመፀኛውና በምድር ላይ ከሚመጣው ጨለማ መዳን ትወዳለህ?

"በጌታ በኢየሱስ ክርቶስ እመን: አንተና ቤተ ሰዎችህም ትድናላች ሁ: ..." (የሐዋሪያት ሥራ 16፥31)

ወዳጄ ሆይ! የዓለም ታሪክ ወደ ማጠ ቃለያው በተቃረበበት በዚህ ጊዜ ይ ህ መልዕክት ወደ አንተ የመጣበት ምክንያት ይኖር ይሆን? ጥፋት ሊ መጣ ነውና ተጠንቀቅ የሚል ማን ነው? ወዳጅ አይደለምን?

ወዳጄ:- እግዚአብሔር ይወድሃል:: በእርግጥ ይህ መልዕክት ከሚወድህ ከእግዚአብሔር ፍቅር የተላከ ነው፤ ይህን ችላ ማለት ራስን መበደል ይሆናል::

እነሆ "በፊታችሁ ሕይወትንና መር ገምን እንዳስቀመጥሁ እኔ ዛሬ ሰማ ይንና ምድርን በአንተ ላይ አስመሰ ክራለሁ : እንግዲህ አንተና ዘርህ በሕይወት ትኖሩ ዘንድ ሕይወትን ምረጥ፤" (ኦሪት ዘዳግም 30፥19)

*************

# የንስሐ ፀሎት

ጌታ እግዚአብሔር ሆይ ! የምሕረትህን መልዕክት አምኜ እ ቀበላለሁ:: እግዚአብሔር ወልድ በመስቀል ላይ የፈጸመውን መስዋዕ ትነት በማመን ማዳኑን እቀበላለሁ: ከዛሬ ጀምሮ ከኃጢአተኛ መንገዴ እመለሳለሁ:: በመንግሥትህ ተቀበ ለኝ አሜን::

*************

⌘⌘⌘⌘⌘⌘

ከእግዚአብሔር ፍቅር ጸጋና ሰላም ይብዛላችሁ::

በዚህ ደብዳቤ ተባርከው ያውቃሉ ? መልክታችን ለፀሎት ወይም ለስብከት አነቃቅቶዎት ያውቃል? ከሆነስ ለመሪዎች፥ መሪ ም ከሆኑ ለምዕመናን አስ ተዋውቀው ያውቃሉ? ይህ ደብዳቤ በአካባቢዎ ቢዳረስ ሊጠቅም አይችል ም? መንፈስ ቅዱስ ምን ያሳስብዎታል? በሚያሳይ ዎት ሁሉ ይተባበሩን:: ማንም ሊሠራ የማይችል በት ጊዜ ሳይመጣ ተባብ ረን ወንጌልን ለዓለም ሁ ሉ ማዳረስ ግድ አለብን:: ጌታ ይባርክዎ::

አድራሻዎቻችን በመግብ ያው ላይ ይገኛሉ::

⌘⌘⌘⌘⌘⌘

ኢየሱስ ጌታ ነው።

ጌታ ይባርክህ።